# የማንነት ጥያቄ ከህገ-መንግስት ድንጋጌዎች አንፃር

ለሚ ዋቄ 04-25-18

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አቢይ አህመድ ከህዝብ ጋር የሚያደርጉትን ውይይት ቀጥለዋል። ባለፈው ሳምንት ማገባደጃ ላይ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጎንደር ከተማ በኋላም በክልሉ ርዕሰ መዲና ባህርዳር ከህዝብ ጋር ተወያይተዋል። በከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣን ደረጃ ከህዝብ ጋር የሚደረግ ውይይት ሁሌም የሚካሄድ ሳይሆን አልፎ አልፎ የሚገኝ ብርቅ ነው፤ በመሆኑም ትኩረትን ይስባል። የሃገር መሪ ከህዝብ ጋር ፊት ለፊት ተቀምጦ የሚያደርገው ውይይት ሃገራዊ መግባባትን፤ በህዝብና በመንግስት መሃከል መተማመንን በመፍጠር ረገድ እጅግ ከፍተኛ ፋይዳ አለው።

በቅድሚያ ከህዝብ ጋር ፊት ለፊት ለመነጋጋር መድፈር የመሪውን ንጽህና ያመለክታል። በሁለተኛ ደረጃ መሪው የህዝቡን ጥያቄና ብሶት አዳምጦ ምላሽ ለመስጠት፣ መፍትሄ ለማበጀት ያለውን ፍላጎትና ቁርጠኝነት ያሳያል። ሃገራዊ መግባባት በመፍጠርና በመንግስትና በህዝብ መሃከል መግበባት በመፍጠር ረገድ ከፍተኛ ፋይዳ የሚኖረው ለዚህ ነው። እናም ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ በየአካባቢው ከህዝብ ጋር የሚያደርጉት ውይይት አሁን ካለው የሃገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ አኳያ ሲታይ ወቅቱን የጠበቀና አስፈላጊ ነው።

የዚህ ጽሁፍ ትኩረት በተለይ ጠቅላይ ምኒስትሩ በጎንደር ያካሄዱት ህዝባዊ ውይይት ነው። በዚህ መድረክ ላይ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ባደረጉት ንግግር ካስተላለፏቸው መልዕክቶች ሊሰመርበት ይገባል ያልኩትን ለመንደርደሪያነት ያህል አነሳለሁ። በማያያዝ በተለይ ልዩ ትኩረት ስቦ የቆየውና አሁንም ትኩረት ሳቢ የሆነው *የወልቃይት የአማራ ማንነት ጥያቄን* በተመለከተ ለተነሳው ጥያቄ ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ የሰጡት ምላሽ ላይ እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ የሚሰማኝን አስተያየት ልሰነዝር ወኳለሁ።

ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ ለጎንደርና አካባቢው ህዝብ ያስተላለፉት መልዕክት ለጎንደር ህዝብ ስነልቦና የሚመጥን ነበር። በዚህ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ንግግር ጎንደሬዎች ራሳቸውን በመስታወት የተመለከቱ ያህል የተሰማቸው ይመስለኛል፤ ለንግግሩ የሰጡት ምላሽ ይህን ስሜት ያሳያልና። ህዝብ በዚህ ደረጃ መሪውን *የእኔ ነው* ብሎ እንዲያስብ የሚያደርግ ንግግርና አቀራረብ እጅግ አስፈላጊ ነው። ጎንደሬዎች ከአሁን በኋላ የፌደራሉም ይሁን የክልላቸው መንግስት ዋጋ የሚሰጣቸው መሆኑ ላይ ዋስትና እንዲያድርባቸው ያደረገ

ይመስለኛል። በዚህ ረገድ ባለፉት ዓመታት ክፍተት ተፈጥሮ እንደነበረ የሚያመለክቱ እውነታዎች መኖራቸውን ልብ ይሏል።

ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ ለጎንደር ህዝብ ባስተላለፉት መልዕክት፤ *ይህ ህዝብ ከሌሎች ወንድሞቹ ጋር በጋራ በመሆን ያፈሰሰውን ደም፣ የከሰከሰውን አጥንት፣ እና የከፈለውን ወደር የለሽ መስዋእትነት የሚመጥን ዴሞክራሲ፣ ልማት፣ ፍትህ እና ሰላም እንዲያገኝ ለማድረግ መንግስት በቁርጠኝነት ይረባረባል* ብለዋል። እውነት ነው ጎንደሬዎች እንደተቀሩት ኢትዮጵያውያን ሃገራቸውን ከጠላት ወረራ ለመከላከል ተዋድቀዋል። ይሁን እንጂ ሁሌም ጎንደር ሲነሳ የሚታወሰን ሌላ መስዋዕትነት አለ፤ በወታደራዊው ደርግ ዘመን የተካሄደው የቀይ ሽብር ዘመቻ ጭፍጨፋ። ወታደራዊው ደርግ ያካሄደው የቀይ ሽብር የጭፍጨፋ ዘመቻ በመላ ሃገሪቱ የተካሄደ ቢሆንም፣ የጎንደር ግን በተለየ የከፋ ነበር። ይህን ሁኔታ የጎንደር እናቶች *መሳኩ ተፈራ የግዜር ታናሽ ወንድም / የዛሬን ማርልኝ ሁለተኛ አልወልድም* በማለት በታሪካዊውና ዘመን አይሽሬው ስንኝ ገልጸውት እንደነበረ ታሪክ ዘግቦ አስቀምጦታል።

ያም ሆነ ይህ፣ በመላ ሃገሪቱ ከተካሄዱት በአስከፊነቱ የሚጠቀሰው በ1960ዎቹ ማገባደጃና በ1970ዎቹ መግቢያ በተካሄደው የቀይ ሽብር የጭፍጨፋ ዘመቻ የተረፉ የጎንደር ወጣቶች በገፍ በለጋ እድሜያቸው ሃገራቸውን ለቀው እንዲሰደዱ ምክንያት ሆኗል። የጎንደር ወጣት ተማሪዎችና አርሶ አደሮች የወሰዱት እርምጃ ስርአቱን መሸሽ ብቻ አልነበረም። ወታደራዊውን ደርግ ባስወገደው ትግል ውስጥም የጎላ ድርሻ ነበራቸው። እናም ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ በንግግራቸው . . . *ያፈሰሰውን ደም፣ የከሰከሰውን አጥንት፣ እና የከፈለውን ወደር የለሽ መስዋእትነት የሚመጥን ዴሞክራሲ፣ ልማት፣ ፍትህ እና ሰላም እንዲያገኝ ለማድረግ መንግስት በቁርጠኝነት ይረባረባል* ማለታቸው ተገቢ ነው።

የጎንደርና አካባቢው ነዋሪዎች ከጠቅላይ ሚኒስትር አብይ ጋር ባካሄዱት ውይይት እንደተቀረው የኢትዮጵያ አካባቢ ሁሉ ሰፋ ያሉ የልማት ጥያቄዎችን አንስተዋል። በሃገሪቱ መረር ያለ ቅሬታ የፈጠረውን የመልካም አስተዳደር መጓደልና ተያያዥ ችግሮችን የሚመለከቱ ጉዳዮችንም አንስተዋል። በሌላ አካባቢ ከሚነሱ ጥያቄዎች የተለየውና አካባቢያዊ የሆነው የወልቃይት ጉዳይም ተነስቷል።

ወልቃይት በሰሜን ጎንደርና በምዕራብ ትግራይ አዋሳኝ አካባቢ ያለ ስፍራ ነው። በዚህ ስፍራ በማናቸውም ሁለት ብሄራዊ ማንነት ያላቸው ህዝቦች የሚኖሩባቸው አካባቢዎች እንደሚሆነው በትግራይና በአማራ ብሄር ተወላጆች መሃከል የደም ትስስር፣ ጠንካራ የኢኮኖሚ ግንኙነት፣ ቋንቋን ጨምሮ የባህል መወራረስ

ወዘተ አለ። በሁለቱ ብሄር ተወላጆች መሃከል ባለው ዘመናትን የተሻገረ አብሮነት የተነሳ፣ በአካባቢው *ማንነቱ ይሄኛው ነው* ብው ቁርጡን መናገር የማይችሉ በርካቶች መኖራቸው እውነት ነው። እንደሁኔታው ሁለቱንም የሚሆኑ ተለዋዋጭ ማንነት (shifting identity) ያላቸውም አሉ፤ አማራም ተጋሩም።

በእንደዚህ አይነት አካባቢ የወሰንና የማንነት ጥያቄ የመነሳት እድሉ ሰፊ ነው፤ ለወልቃይት ልዩ አይደለም። በኦሮሚያና በሲዳማ፣ በኦሮሚያና በኢትዮጵያ ሱማሌ፣ በአፋርና ኢትዮጵያ ሱማሌ ወዘተ መሃከልም ሲነሳ ቆይቷል፤ ለወደፊትም ይነሳል። እናም ከወልቃይት ጋር በተያያዘ የወሰንም ይሁን የማንነት ጥያቄ መነሳቱ እንግዳ ነገር አይደለም። የኢፌዴሪ ህገመንግስትም የዚህ አይነት ጥየቄዎችን የሚያስተናግድበትና መፍትሄ የመያበጅበትን ድንጋጌ ይዟል፤ የክልል መንግስታት ህገመንግስቶችም እንዲሁ።

ባለፉት ዓመታት *የወልቃይት ጉዳይ/ጥያቄ* የሚባለው ለብዙ ኢትዮጵያውያን ግልጽ አልነበረም። ጉዳዩ አንዳንዴ የወሰን፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ የማንነት እየመሰለ ስለሚቀርብ ነው ግልጽ ያልሆነው። አሁንም ብዙ ኢትዮጵያውያን ጉዳዩን በግልጽ አያውቁትም። ጥያቄውን በግልጽ ማስቀመጥ ቀዳሚው ተግባር መሆኑን ማስታወስ ተገቢ ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ ሌላው ግልጽ ያልሆነ ጉዳይ የጥያቄው አቅራቢ አካል ነው። የዚህ አይነት ጥያቄ - የወሰንም ይሁን የማንነት ጥያቄ የሚቀርበው፣ ጥያቄው ተነሳበት የተባለበት አካባቢ በሚኖሩ ዜጎች ሆኖ ሳለ፣ የአካባቢው ነዋሪ ያልሆኑ ሰዎች ባለጉዳይ ሆነው የሚታዩበት ሁኔታ ያለ ይመስላል። ይህ፣ ጉዳዩን በህገመንግስታዊ መንገድ የመፍታቱን ተግባር እንዳያወሳሰበው ያሰጋል። ስለዚህ የጉዳዩ ባለቤት በግልጽ ሊታወቅ ይገባል።

ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ ሰሞኑን ከጎንደር ነዋሪዎች ጋር ባደረጉት ውይይት ላይ ለተነሳው ወልቃይትን የተመለከተ ጥያቄ በሰጡት ምላሽ፤ *የወልቃይት የማንነት ጥያቄ ልክ በሌሎች አካባቢዎች እንደሚነሳው ጥያቄ ሁሉ በህገመንግስቱ መሰረት የሚታይ ይሆናል* ብለዋል።

ይህን ጉዳይ ከወሰንም ከማንነትም አኳያ ያለውን ህገመንግስታዊ አንድምታ እንመልከት። የኢፌዴሪ ህገመንግስት አንቀጽ 48 "የአከላለል ለውጦች" በሚል ርዕስ ስር፤

> *የክልሎችን ወሰን በሚመለከት ጥያቄ የተነሳ እንደሆነ፣ ጉዳዩ በሚመለከታቸው ክልሎች ስምምነት ይፈጸማል። የሚመለከታቸው ክልሎች መስማማት ካልቻሉ፣ የፌዴሬሽኑ*

*ምክር ቤት የህዝቡን አሰፋፈርና ፍላጎት መሰረት በማደረግ ይወስናል።*

ይላል።

እንግዲህ፣ የወልቃይት ጥያቄ የወሰን ጥያቄ ከሆነ የአማራና የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስታት በመነጋገር፣ የወሰን ጥያቄው ከተነሳበት አካባቢ ነዋሪዎች ጋር በመወያየት ሊፈቱት ይችላሉ። በዚህ ዙሪያ ከዚህ ቀደም የሁለቱ ክልሎች ርዕሳነ መስተዳድሮች በተገኙበት የአካባቢውን ነዋሪዎች ያሳተፈ ውይይተ ተካሂዶ ወሰን የማካለል ስራ መከናወኑ ይታወሳል። እርግጥ፣ ይህን ከህዝብ ጋር በመወያየት የተካሄደ አወሳሰን የማይቀበሉ ሊኖሩ ይችላሉ። አወሳሰኑን የማይቀበሉ የአካባቢው ነዋሪዎች ካሉ፣ በህገመንግስቱ መሰረት ሁለቱ ክልሎች ጉዳዩን ዳግም እንዲመለከቱት ሊጠይቁ ይችላሉ። ክልሎቹ መስማማት ካልቻሉ ደግሞ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በህዝበ ውሳኔ በሚረጋገጥ የህዝብ ፍላጎት መሰረት ጉዳዩን እንዲፈታ ማደረግ ይቻላል። ስለዚህ ጉዳዩ ዳግም መነሳቱ በራሱ ችግር አይደለም።

በወልቀይት የሚኖሩ የአማራ ብሄር ተወላጆች ያነሱት ወይም አነሱ የተባለው የማንነት ጥያቄም ከሆነ ጥያቄው መፍትሄ የሚያገኝበት ህገመንግስታዊ አግባብ አለ። የኢፌዴሪ ህገመንግስት አንቀጽ 47 *የፌደራል መንግስት አባላት* በሚል ርዕስ ስር በንኡስ አንቀጽ 1 ላይ ዘጠኙን ብሄራዊ ክልላዊ መንግስታት ዘርዝሮ፣ በቀጣይ ንኡሳን አንቀጾቹ፤

- *በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተመለከቱት ክልሎች ውስጥ የተካተቱ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦች፣ ሕዝቦች በማንኛውም ጊዜ የየራሳቸውን ክልል የማቋቋም መብት አላቸው፤*
- *የማንኛውም ብሄር፣ ብሄረሰብ፣ ሕዝብ የራሱን ክልል የመመሰረት መብት ስራ ላይ የሚውለው፤*

*ሀ. የክልል መመስረት ጥያቄው በብሄሩ፣ በብሄረሰቡ ወይም በህዝቡ ምክር ቤት በሁለት ሶስተኛ ድምጽ ተቀባይነት ማግኘቱ ሲረጋገጥና ጥያቄው በጽሁፍ ለክልሉ ምክር ቤት ሲቀርብ፤*
*ለ. ጥያቄው የቀረበለት የክልል ምክር ቤት ጥያቄው በደረሰው በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ለጠየቀው ብሄር፣ ብሄረሰብ፣ ወይም ህዝብ ህዝበ ውሳኔ ሲያደራጅ፤*
*ሐ. ክልል የመመስረት ጥያቄው በብሄሩ፣ በብሄረሰቡ ወይም ሕዝቡ ሕዝበ ውሳኔ በአብላጫ ድምጽ ሲደገፍ፤*

ይላል።

ይህን የህገመንግስት ድንጋጌ ከአፈጻጸም አኳያ፣ በደቡብ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል በስልጤ ብሄር ጥያቄ፤ እንዲሁም በአማራ ክልል በቅማንት ህዝብ ጥያቄ እንዳየነው ክልል መመስረትን ብቻ ሳይሆን፣ በዞንም ይሁን በወረዳ ደረጃ ራስን በራስ የማስተዳደር መዋቅርን መመስረትን ያጠቃልላል።

እንግዲህ የወልቃይት ጉዳይ ትግራይ ክልል ውስጥ የሚኖሩ የአማራ ብሄር ተወላጆች ያነሱት የአማራ የማንነት ጥያቄ ከሆነ፣ በህገመንግስቱ መሰረት ጥያቄው በቅድሚያ የሚቀርበው ጥያቄውን ያነሳው የአማራ ህዝብ ለሚኖርበት ወረዳ ወይም ሌላ መዋቅር የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነው። ይህ ምክር ቤት ጥያቄውን በሁለት ሶስተኛ ድምጽ ከደገፈው ጉዳዩ ለትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይቀርባል። ጥያቄው የሚደርሰው የትግራይ የክልል ምክር ቤት ጉዳዩን ራሱ ውሳኔ አያሳልፍበትም። ከዚህ ይልቅ፣ ጥያቄው በተነሳበት አካባቢ ህዝበ ውሳኔ ያደራጃል። በህዝበ ውሳኔው የአማራነት የማንነት ጥያቄው በአብላጫ ድምጽ ድጋፍ ካገኘ የአማራ ማንነት ጥያቄውን ያቀረበው ህዝብ ራሱን በራሱ የሚያስተዳድርበት መዋቅር ያደራጃል። ከዚህ በኋላ የህገመንግስት ትርጓሜ የሚሻ ጉዳይ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በህዝበ ውሳኔ ራሱን የሚያስተዳድርበት መዋቅር የዘረጋው የአማራ ህዝብ ከአዋሳኙ የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጋር ሊዋሃድ የሚችልበት ሁኔታ ይኖር ይሆናል።

ከማንነትም ሆነ ከወሰን ጋር የተያያዘ ጥያቄ ህገመንግስታዊ አፈታት ከላይ በአጭሩ የተጠቀሰውን ይመስላል። የወልቃይት ጉዳይም በዚህ አግባብ ነው የሚፈታው። ይህ ህገመንግስታዊ ድንጋጌ የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦች እና ሕዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው እያስተዳደሩ በእኩልነትና በመከባበር ላይ በተመሰረተ አንድነት ለመኖር ያበጁት ነው። ድንጋጌውም በኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ይሁንታ የጸደቀ ነው። ይህ ድንጋጌ ሃገር ማንም ተነስቶ *ከዚህ ወዲያ የእኔ* ብሎ የሚከልለው መሬት ሳይሆን፤ ጥቅምና ፍላጎት፣ መብትና ነጻነት ያለው ህዝብ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው።